በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Development

ቁጥር 7/ኪ/11/1/23
Ref.No
ቀን
Date

ለትራንስፖርት ሚኒስቴር

ለትራንስፖርት ባለስልጣን

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ለአዲስ አበባ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ

<u>አዲስ አበባ</u>

ለረጅም ጊዜያት አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተው በእርጅና፣ በብልሽትና በመለዋወጫ እጦት ምክንያት በመቆማቸው በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በኩል በጨረታ እንዲወገዱ የሚደረጉ ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት ስም ወደ ገዥ ለማዛወር የሚያስችል መረጃዎች በተሟላ መልኩ ስለማይገኙ ቀልጣፋ አገልግሎት ለባለጉዳዮች ስለማይሰጥ ከፍተኛ ቅሬታዎች እየተነሱ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ ተሽከርካሪዎች ከመነሻው በትራንስፖርት ጽ/ቤቶች ምዝገባ ያላደረጉና ምዝገባ ያደረጉም ቢሆን የተሟላ መረጃ የሌላቸው በመሆኑ በተለያዩ የፌዴራል መ/ቤቶች ያለ አገልግሎት ቆመው የሚገኙ ቢሆኑም ማስወገድ አልተቻለም፡፡

በተለይም የመንግስት መ/ቤቶች ሲዋሃዱ፣ ሲነጣጠሉ እንዲሁም የአንድ የመንግስት መ/ቤት ተሽከርካሪ ወደ ሌላ የመንግስት መ/ቤት ሲተላለፍ ንብረቱ እና የንብረቱ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትሎ እንዲተላለፍ ስለማይደረግ ለችግሩ መባባስ ዓቢይ ምክንያት ሆኗል፡፡

በመሆኑም መንግስት ያገለገሉ ተሽከርካሪዎችን በወቅቱ በማስወገድ ለንብረቱ ተገቢውን ዋጋ እንዲያገኝ ለማድረግ ይህንን ችግር መፍታት ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል ፡፡

ስለሆነም፡-

ከመንግስት መ/ቤቶች ተሰባስበው በጨረታ ሽያጭ ከሚወገዱ ተሽከርካሪዎች መካከል

1. ለምዝገባ ከሚያስፈልጉ ሰነዶች ውስጥ ዋነኛው ዲክላራሲዮን የሌላቸው ከሆነ

ሀ/. ቀደም ሲል በየትኛውም የትራንስፖርት ጽ/ቤት በኩል ምዝገባ ያላደረጉ ሊብሬና ሰሌዳ ያልተሰጣቸው በአዲስ መልክ ለመመዝገብ ምንም አይነት ሰነድ የሌላቸው ተሽከርካሪዎች ሰነድ አልባ ስለመሆናቸው የሚገልጽ ከመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በኩል በደብዳቤ ሲገለጽ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ለገዥዎች የዜሮ ዲክላራሲዮን ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው ፤

ለ/. ቀደም ሲል በትራንስፖርት ጽ/ቤቶች በኩል ምዝገባ የፈፀሙ ሌብሬና ሰሌዳ የተሰጣቸው ተሽከርካሪዎች በፋይላቸው ውስጥ የዲክላራሲዩን ቁጥርም ሆነ ሰነድ የሌላቸው ከሆነ በፊደል "ሀ" መሠረት የዜሮ ዲክላራሲዮን በገዥዎች ስም ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው፤

ሐ/. ተሽከርካሪዎች ከቀረጥ ነፃ የገቡ ከሆነና ከ10 ዓመት በላይ ከሆናቸው ቀዳሚ ዲክላራሲዮን ካላቸው በሰነዳቸው መሠረት ዲክላራሲዮን እንዲዘጋጅላቸው እንዲደረግ፤ ዲክላራሲዮን በሰነድም ሆነ በቁጥር ካልተገኘ በፊደል "ሀ" እና "ለ" መሠረት በገዥዎች ስም ዜሮ ዲክላራሲዮን እንዲዘጋጅ ፤

መ./ ከፊደል ተራ ሀ- ሐ በተመለከተው መንገድ ተዘጋጅቶ የሚቀርበውን ዲክላራሲዮን ተቀብሎ የትራንስፖርት ጽ/ቤት የምዝገባና የስም ዝውውር አገልግሎት እንዲፈፀም ፤

2. ምዝገባ አድርገው ሌብሬና ሰሌዳ ቢወስዱም

ሀ./ ሊብሬው ወይም ሰሌዳው ወይም ሁለቱም የጠፋ ከሆነ የመንግስት ተሽከርካሪዎች በጨረታ ሲወገዱ ገዥዎች ተሽከርካሪ በስማቸው እንዲመዘገብላቸው ሲጠይቁ ሊብሬ ወይም ሰሌዳ ወይም ሁለቱም የጠፋ መሆኑን ተሽከርካሪው በስሙ የተመዘገበለት ወይም ተሽከርካሪው በንብረትነት

ተረክቦ የሸጠው የመንግስት መ/ቤት ሊብሬ ወይም ሰሌዳው ወይም ሁለቱም መጥፋቱን በደብዳቤ ከገለፀ የተሽከርካሪው ፋይል የሚገኝበት የትራንስፖርት ጽ/ቤት ስለጠፋው ሊብሬ ወይም ሰሌዳ ከፖሊስ መረጃ መቅረብና በጋዜጣ ማስታወቂያ እንዲወጣ ማድረግ ሳያስፈልግ የጠፋውን ሰሌዳ /ሊብሬው የሚገልፀውን ደብዳቤ ፋይሉ ውስጥ በማያያዝ ብቻ ለገዥው አገልግሎት እንዲሰጥ ፤

ለ/. በሊብሬው ወይም በተሽከርካሪው ምዝገባ መረጃ ላይ ያለው የባለንብረት ስም ተሽከርካሪው በሽያጭ እንዲወገድ ካደረገው የመንግስት መስሪያ ቤት ቢለያዩ እንኳ ንብረቱን ሲገለገልበት ቆይቶ በሽያጭ እንዲወገድ ያደረገው የመንግስት መ/ቤት በተሽከርካሪው ላይ ኃላፊነቱ የራሱ መሆኑን የሚያረጋግጥ የግዴታ ደብዳቤ ለሻጩ በመስጠት ለሚነሳው የባለቤትነት ጥያቄ ዋቢ መሆኑን ሲያረጋግጥ የስም ዝውውሩ እንዲፈፀም ፣

በዚህ መሠረት ውሳኔው ተግባራዊ እንዲደረግ እየጠየቅን፣ ለየመ/ቤቶቻችሁ ተጠሪ የሆኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይህንኑ አውቀው ውሳኔውን ሥራ ላይ እንዲያውሉ እንዲገለጽላቸው እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፣

- ለመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ
- ለመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት

አዲስ አበባ

ገ/ኢ/ል/ሚ

/አጥ